# የውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ ሲሰጥ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

Public Health
Seattle & King County

ውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ የሚሰጠው ሊጎዱ የሚችሉ ባክቴሪያ ወይም ሌሎች ፍጥረታት በውሃ አቅርቦቱ ውስጥ ሲገኙ ነው። ውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉም የምግብ ተቋሞች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው።

## 1 ክንዋኔዎችን ማቆም

- ይህ ማለት፦ ትእዛዙ እስኪነሳ ድረስ ሁሉንም የምግብ አገልግሎቶች ያቁሙ
- ማብሰል፣ የምግብ ዝግጅት እንዲሁም ማጠብን ጨምሮ




## 2 በውሃውን ያፍሉ ትእዛዙ ወቅት

- እጅን መታጠብ
  - -እጆችዎን በሳሙና እና ለብ ባለ ውሃ ለ 20 ሴክንዶች ይታጠቡ
  - -እጆችዎን በንጹህ የወረቀት ፎጣዎች ያድርቁ
  - -ከታጠቡ በኋላ፣ የእጅ ማጥሪያ ይጠቀሙ
- ታጥበው የነበሩ ትኩስ ምርቶችን ሁሉ ይጣሉ
- ማንኛውንም ህመም ለህዝብ ጤና ክፍል ያስታውቁ 206-296-4774









## 3 ትእዛዙ ከተነሳ በኋላ

- ሁሉንም የውሃ መስመሮች ለ 5 ደቂቃ ያህል ውሃ ይልቀቁባቸው
- ምግብ የሚነካቸውን ሲንኮች እና ቦታዎች ይጠቡ፣ ያለቅልቁ እንዲሁም በማጽጃ ፈሳሽ ያጽዱ
- የበረዶ መስሪያዎችን ባዶ ያድርጉና ውሃ ይልቀቁባቸው፣ ውስጣቸውን በማጽጃ ፈሳሽ ያጽዱ፣ መጀመሪያ የሚወጣውን በረዶ ይጣሉት
- የመጠጥ ማሽኖችን ፈሳሻቸውን ከውስጣቸው ያድርቁ እና ይጥቡ፣ መስመሮቹን ያለቅልቁና በፈሳሽ ማጽጃ ያጽዱ
- የሰሃን ማጠቢያ ማሽኖችን ባዶዋቸውን ለሁለት ዙሮች ያሰሩ
- ሁሉንም ድስቶች፣ ኩባያዎች እና ሰሃኖች ይጠቡ፣ ያለቅልቁ እና በማጽጃ ፈሳሽ ያጽዱ







## 4 ዳግም መክፈቻ መመሪያዎች

ለዳግም መከፈት ፍተሻ/ፍቃድ የህዝብ ጤና ክፍልን ያናግሩ፡

206-263-9566 (Seattle)

206-477-8050 (Bellevue)




ዝርዝር መመሪያዎችን ለማግኘት ሌላኛውን ጎን ይመልከቱ።

# ዝርዝር መመሪያ ለውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ እና ለምግብ ተቋሞች

ሁሉም የምግብ ተቋሞች በውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-

ስለ ቅደም ተከተሎች ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት፣ የህዝብ ጤና ክፍልን በ 206-263-9566 (Seattle), 206-477-8050 (Bellevue) ያግኙ፡፡

## 1 ክንዋኔዎችን ማቆም

- ውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ የሚሰጠው ሊጎዱ የሚችሉ ባክቴሪያ ወይም ሌሎች ፍጥረታት በውሃ አቅርቦቱ ውስጥ ሲገኙ ነው።
- ትእዛዙ እስኪነሳ ድረስ ሁሉንም የምግብ አገልግሎቶች እንቅስቃሴዎች ማቆም ያስፈልጎዎታል።
- የአካባቢው የውሃ እና የጤና ክፍሎች ውሃው አስተማማኝ የመጠጥ ውሃ ደረጃዎችን እንደሚያሟላ እስኪወስኑ ድረስ ማንኛውም የምግብ አገልግሎት እንቅስቃሴን እንዳይቀጥሉ።

## 2 በ ውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ ወቅት

- ሁሉንም የመጠጥ ውሃ ምንጮች ያግዱና እንዲሁም ሁሉንም በረዶዎች ይጣሉ
- ከትእዛዙ በፊት የታጠቡ ማንኛውም ምርቶች (አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ እና ቅጠላ ቅጠሎች) መጣል አለባቸው።
- እጆችዎን በሳሙና እና ለብ ባለ ውሃ ለ 20 ሴክንዶች ይታጠቡ። በንጹህ የወረቀት ፎጣዎች ያድርቁ። በእጅ ማጥሪያ መጠቀምን ያስከትሉ። ለመብላት ዝግጁ የሆኑ ምግቦችን በባዶ እጅ መንካትን አይፍቀዱ።
- በተወሰነ የምግብ ዝርዝር የመስራት እድል ሊኖር ይችላል፣ የእርስዎ ተቋም ብቁ መሆኑን ለማወቅ የህዝብ ጤና ክፍልን ያናግሩ

## 3 የውሃውን ያፍሉ ትእዛዝ ከተነሳ በኋላ

ሁሉንም የውሃ መስመሮች ለ 5 ደቂቃ ያህል ውሃ ይልቀቁባቸው እነኚህ ላይ ውሃ መልቀቅ ያስታውሱ፡- ቧንቧዎች፣ በረዶ መስሪያዎች፣ የመጠጥ ማሽኖች፣ ሰሃን ማጠቢያዎች፣ እንዲሁም የቧንቧ ውኃ የሚጠቀሙ ሌሎች ስርዓቶች ላይ ሁሉ።

- የበረዶ መስሪያዎን ይጠቡ እና በማጥሪያ ፈሳሽ ያጽዱት። መጀመሪያ የሚወጣውን በረዶ ይጣሉት*
- የቧንቧ ውሃ የሚጠቀሙ የመጠጥ ማሽኖች መድረቅና ውሃ ሊለቀቅባቸው ያስፈልጋል።
- የሰሃን ማጠቢያ ማሽኖችን ባዶዋቸውን ቢያንስ ለሁለት ዙሮች ያሰሩዋቸው። የሰሃን ማጠቢያ ማሽንዎ በትክክል እየሰራ መሆኑን የኬሚካል ማጽጃውን በተገቢው የምርመራ ቁራጭ ወረቀቶች (ከ 50 – 100 ppm ለክሎሪን) ወይም የውሃውን የሙቀት መጠን በ ጌጁ ላይ በማየት (180° F)።
- መገልገያ መሳሪያዎች ፣ ኩባያዎች እና ሰሃኖች በድጋሚ መታጠብ፣ መለቅለቅ እንዲሁም በማጥሪያ ፈሳሽ መለቅለቅ አለባቸው።
- የወራጅ ውሃ ጥልቅ ጉርጓዶች በውሃ መጽዳት አለባቸው። ጉርጓዶቹ አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት መድረቅ፣ መለቅለቅ እንዲሁም በማጽጃ ፈሳሽ መጽዳት ይኖርባቸዋል።

## 4 ድጋሚ መክፈት

ከመክፈትዎ በፊት የሕዝብ ጤና ክፍልን በ 206-263-9566 (Seattle), 206-477-8050 (Bellevue)ያነጋግሩ።

2304_13264w_DPH_fact_boil_waterAMH.ai